**ማሳሰቢያ፦ የቦርድ ኮሚቴ ስለ ቨርቹወል ትምህርት የማኅበረሰብ ውይይት ያደርጋል**

የትምህርት ቦርድ የኮሙኒኬሽን እና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ኮሚቴ ሰኞ፣ ኦክቶበር 19 ስለ ቨርቹወል ትምህርት ከ 6–7:30 p.m. የማህበረሰብ ውይይት ያካሄዳል።

በዚህ በይነመረብ ላይ ለመከታተል ይችላሉ፦  www.montgomeryschoolsmd.org, youtube.com/mcpstv ወይም በ፦ MCPS-TV (Comcast 33, Verizon 36 እና RCN 88)። በዚህ አውታረመረብ ላይ ጥያቄዎችን በቅድሚያ ለማቅረብ ይችላሉ፦ www.mcpssubmitquestion.org።

**WXY አብሮ አሳታፊ የሆነ ወሰን የማካለል መገልገያ (Tool) ይዘረጋል**

ዲስትሪክት አቀፍ የማካለል ሁለተኛው ምዕራፍ ትንተና የሚያተኩረው በአሳታፊ የማካለል ዳሰሳ መሣሪያ (tool) በመሣተፍ ላይ ሲሆን፥ የ MCPS ባለድርሻ አካላት ስለትምህርት ቤት ማካለል በጥልቀት እንዲመለከቱ እና የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል። መሣሪያው የተዘጋጀው ከዲስትሪክቱ ጋር በቀጥታ በሚሠራ አካል "WXY Studios (WXY)" እንደመሆኑ ለ MCPS ወሰን የማካለል ትንታኔ መረጃዎችን ከተለያየ አቅጣጫ - በተለያየ እይታ ለማገናዘብ እንዲቻል ለማድረግ ነው።

ማርች ላይ በቀረበው ጊዜያዊ ሪፖርት ስለ መረጃ ትንተናው አጠቃቀም፣ ስለብዝሃነት እና የቦታ ቅርበት ቁልፍ የሆኑ እሳቤዎችን አጉልቶ አሳይቷል። በተጨማሪም ሪፖርቱ ከሌሎች የትምህርት ቤቶች ዲስትሪክቶች የተገኘ በተወሰነ ርቀት ስለወሰን ማካለል በማነጻጸሪያነት መረጃዎችን እና ማኅበረሰቡን በማሳተፍ የተደረገውን የማጠቃለያ ሪፖርት ያካትታል።

ስለዚሁ አሳታፊ መገልገያ መሣሪያ (tool) ማክሰኞ፣ ኦክቶበር 20 እና ሐሙስ፣ ኦክቶበር 22 ከ 7–8:30 p.m. በሚካሄዱት ሁለት ቨርቹወል ህዝባዊ ኦንላይን የበይነመረብ ውይይት (ዌብናሮች) የማህበረሰብ ስብሰባዎች ላይ መግለጫ ይሰጣል። በተጨማሪም እሮብ፣ ኦክቶበር 28 ከ 7–9 p.m. የ WXY እና MCPS መሪዎች ስለመሣሪያው (tool) አጠቃቀም ከማህበረሰቡ ግብረመልስ ለማግኘት ቨርቹወል የማህበረሰብ ስብሰባ ይደረጋል። ስብሰባዎቹ በጠቅላላ በዙም "Zoom" የሚካሄዱ ስለሆነ መመዝገብ ያስፈልጋል። በስብሰባው ላይ መገኘት የማይችሉ ሰዎች ኩነቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የተቀዳውን ኦንላይን የበይነመረብ ውይይት (ዌብናር) መመልከት ይችላሉ።

ኩነቶቹ ላይ ለመሣተፍ ይመዝገቡ

በተጨማሪም WXY ከትምህርት ቤት ርእሰመምህራን እና ከተማሪዎች ጋር አሳታፊ ኩነቶችን ያካሄዳል፣ እንዲሁም ብዙ ጊዜ ለመገኘት ከማይችሉ ማህበረሰቦች ጋር በአነስተኛ ቡድን ስብሰባዎችን ይደረጋሉ።

ስለ ማካለል ትንታኔ ይበልጥ ግንዛቤ ያግኙ

**ለካውንቲው ነዋሪዎች የኮቪድ-19 የኪራይ እፎይታ ፕሮግራም**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት (DHHS) በኮቪድ-19 ምክንያት የፋይናንስ ክስረት ለደረሰባቸው መስፈርት የማሟላት ብቃት ያላቸው ቤተሰቦች የአጭር ጊዜ የኪራይ እፎይታ ድጋፍ ይሰጣል። ፕሮግራሙ ፈንድ በተገኘ መጠን፣ ብቃት ለሚኖራቸው ቤተሰብ የኪራይ ውዝፍ ለመክፈል እና/ወይም ለመጪዎቹ ወራት ኪራይ የሚከፈል እስከ $4,000 ይሰጣል። ፕሮግራሙ ፈንድ የሚያገኘው ለጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት (DHHS) ከተመደበው $20 ሚሊዮን የበጀት ድጋፍ ነው።

ይበልጥ ግንዛቤ ለማግኘት እና ለኪራይ እፎይታ ድጋፍ ፕሮግራም በዚህ ድረገጽ ላይ ማመልከት ይችላሉ።

**< ኦክቶበር 26 - 31 የሚካሄደው የአእምሮ ጤንነት ግንዛቤ ማስጨበጥ ሣምንት እንዳያመልጥዎት**

እንደነውር ማግለል ያብቃ። እስቲ ስለ አእምሮ ጤንነት እንነጋገር።

MCPS ስለ አእምሮ ጤንነት የግንዛቤ መስጫ ሣምንት ከኦክቶበር 26 - 31 የሚያካሄድ ሲሆን ይኼውም ለአንድ ሣምንት የሚዘልቅ ኤክስፖ፣ በዙም (Zoom) የሚካሄድ አውደጥናቶችን፣ የሪሶርሶች አውደ ርእይ፣ የውይይት ጊዜያትን እና የጥያቄና መልስ ክፍለጊዜዎችን ያካትታል። አንዳንድ አውደጥናቶች በተለያዩ ቋንቋዎች ይገኛሉ። በሳምንቱ ውስጥ የሚደረጉት ዐውደ ጥናቶች እና እንቅስቃሴዎች በሙሉ ቨርቹወል የሚካሄዱ ናቸው።

በ MCPS እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሳይኮሎጂ ባለሙያዎች ማህበር የሚዘጋጀው ነጻ ሁነት ለሠራተኞች፣ ለተማሪዎች እና ለቤተሰቦቻቸው ክፍት ነው።

ሣምንቱ የሚጀምረው ሰኞ፣ ኦክቶበር 26 በ 7 p.m. ሲሆን በ "National Center for School Mental Health at the University of Maryland School of Medicine፣ ተባባሪ ፕሮፌሰር እና ዋና የፋኩልቲ አባል በሆኑት "Jill Haak Bohnenkamp" አማካይነት በሚሰጥ የመክፈቻ ንግግር የሚከፈት ይሆናል።

በእያንዳንዱ ቀን የውይይት ፕሮግራሞችና በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የሚቀርቡ ቪዲዮዎች ይቀርባሉ። ርእሶቹ በዘመነ ኮቪድ-19 ደስታን ስለመሻት፣ ማህበራዊ ሚድያ፣ ራስን ስለመግደል ግንዛቤ እና መከላከል፣ ጤናማ አኗኗር፣ ከለውጥ ጋር መላመድ፣ የአካል እንቅስቃሴ የሚያሳድረው ተፅእኖ፣ ስልጡን የሳይበር አጠቃቀም፣ እና በፍቅረኛሞች ውሎ ስለሚከሰት ግጭት ያካትታል።

ሣምንቱ የሚጠናቀቀው ቅዳሜ፣ ኦክቶበር 31 በቨርቹወል ሪሶርስ አውደ ርእይ እና በጥያቄ እና መልስ የቪድኦ ጭውውት (webinar) ይሆናል። በጠቅላላ የማህበረሰብ አባላት ይህንን ከእኩለ ቀን እስከ 1:30 p.m. በዙም "Zoom" የሚካሄድ ኩነት እንዲሣተፉ ተጋብዘዋል። የሣምንቱን ኩነቶች የሚያሣይ ጠቅላላ መርሃግብር እዚህ ይገኛል።

"promo video" ይመልከቱ

የሪሶርስ አውደ ርእይ በሚደረግበት ወቅት፥ በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎችና መንግሥታዊ ድርጅቶች መረጃዎችን ይሰጣሉ። ከእነርሱም መካከል "Montgomery County Department of Health and Human Services፥ EveryMind፥ RAP/The Landing፥ Family Services, Inc.፥ BTheOne፥ Montgomery County Crisis Center፥ Caring Matters and Our Minds Matter" ይገኙበታል።

የ MCPS ተማሪዎች ስለ አእምሮ ጤንነት የግንዛቤ መስጫ አክቲቪቲዎች ላይ ቨርቹወል የሚሳተፉ ከሆነ፣ ውይይት በተደረገባቸው አንኳር ርእሶች ላይ አቀንቃኝ በመሆናቸው እና ግንዛቤ በማስጨበጥ እስከ አምስት የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) ሠዓቶችን ለማግኘት ይችላሉ። ተማሪዎቹ ትምህርቱን እንዲያዳምጡና በጉግል ቅጽ እንዲሞሉ የሚጠየቁ ሲሆን በተማሩት መረጃ ላይ እና ያገኙትን መረጃ በትምህርት ቤታቸው ለሚገኘው ማህበረሰብ እንዴት እንደሚጠቀሙበት ያትታሉ።

ስለ አእምሮ ጤንነት የግንዛቤ ሣምንት

**ስለ መከባበር እንነጋገር የተሰኘ ታወን ሆል - Town Hall የውይይት መድረክ ሪኮርድ ለማድረግ አሁን ዝግጁ ነው**

"Let's Talk Respect" አምልጦት ከሆነ፦ ጾታዊ ትንኮሳን እና ጥቃትን ስለመከላከል ኦክቶበር 13 የተካሄደ ውይይት ታወን ሆል-Town Hall ሪኮርድ የተደረገውን እዚህ ይመልከቱ።

ለተማሪዎች እና ለማህበረሰብ መድረክ ለመስጠት፣ MCPS ከሚከተሉት የመንግስት ድርጅቶችና ተቋማት ጋር በትብብር የውይይት መድረክ አዘጋጅቷል፦ "Montgomery County State's Attorney's Office, the Montgomery County Police Department, the Victim Assistance Sexual Assault Program, Choose Respect Montgomery, Coaching Boys Into Men, EveryMind and Identity, Inc."

- በማህበራዊ ሚድያ ለሚጋሩት የተማሪ ታሪኮች እውቅና ስለመስጠት

- የ MCPS ምላሾችን እና ወቅታዊ መግለጫዎችን ያጋሩ (ፈጣን፣ የአጭር ጊዜ እና የረዥም ጊዜ ተግባሮች)
- ተማሪዎች ጥያቄ ለመጠየቅ እንዲችሉ ማንነት የማይገለፅበት፣ አስተማማኝ ቦታ መስጠት
- በፆታዊ ጥቃትና ትንኮሳ የተጠቁ ተማሪዎችን በተሻለ ሁኔታ መደገፍ ስለሚቻልበት ስልት የተማሪ ግብረመልስ ማሰባሰብ
- ተማሪዎችንና ቤተሰቦችን ከተገቢው ሪሶርስ ጋር ማገናኘት

የውይይት አቅራቢዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

- **Lisette Dardon,** Site Manager, Watkins Mill High School Wellness Center, Identity, Inc.
- **Captain Amy Daum,** Director, Montgomery County Police Department Special Victims Unit
- **Debbie Feinstein,** Chief of the Special Victims Unit, Montgomery County State's Attorney's Office
- **Rachel Larkin,** Director, Crisis Prevention and Intervention, EveryMind
- **Jason Lomax,** Teacher and Varsity Football Coach, Rockville High School
- **Rafiah Prince**, Victim Assistance Sexual Assault Program
- **Ed Clarke**, Chief Safety Officer for MCPS
- **Greg Edmundson**, Director, Student Welfare and Compliance
- **Ed Reed** ፣ Resource Counselor, Robert Frost Middle School